# ምዕራፍ 10

# የኢትዮጵያ ገንዘቦች

## 10.1 የኢትዮጵያ ሳንቲሞችና የብር ኖቶች

### ሣንቲሞች

የኢትዮጵያ ገንዘብ ምስላቸው ከዚህ በታች የተመለከተው ሁሉ የኢትዮጵያ ሳንቲሞች (የሳንቲም ዲናሮች) ናቸው።

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
|  |  |  |  |  |  |
| አንድ ሣንቲም | አምስት ሣንቲም | አሥር ሣንቲም | ሃያ አምስት ሣንቲም | ሃምሣ ሣንቲም | የአንድ ብር ሣንቲም |

**አስተውሉ** ሁሉም ሣንቲሞች የፊትና የጀርባ ምስሎች አሏቸው።





የ1 ባለ 5 ሣንቲም ዲናር በ5 የባለ አንድ ሣንቲም ዲናሮች ይለወጣል ወይም ይመነዘራል።



አንድ ባለ 10 ሣንቲም ዲናር በ2 የባለ አምሥት ሣንቲም ዲናሮች ይለወጣል ወይም ይመነዘራል።



አንድ ባለ 50 ሣንቲም ዲናር በ2 የባለ 25 ሣንቲም ዲናሮች ይለወጣል ወይም ይመነዘራል።



አንድ ባለ 50 ሣንቲም ዲናር በ5 የባለ 10 ሣንቲም ዲናሮች ይለወጣል ወይም ይመነዘራል።

## የቤት ሥራ

አንድ የቤተሰባችሁን አባል በመጠየቅ የኢትዮጵያን የሣንቲም ገንዘቦች ዓይነትና ምንዛሪ ዘርዝራችሁ ለቡድን አባሎቻችሁ አቅርቡ።

### መልመጃ

1. ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ።

ሀ. አንድ ባለ 10 ሣንቲም ዲናር በስንት ባለ 1 ሣንቲም ዲናሮች ይመነዘራል?

ለ. አንድ ባለ 25 ሣንቲም ዲናር በስንት ባለ 5 ሣንቲም ዲናሮች ይመነዘራል?

ሐ. አንድ ባለ 50 ሣንቲም ዲናር በስንት ባለ 5 ሣንቲም ዲናሮች ይመነዘራል?

© MoE, FDR Ethiopia Not to be republished

## 2. ሠንጠረዡን በምሳሌው መሠረት ሙሉ።

| የተሰጡት የሣንቲም ዲናሮች | በባለ 1 ሣንቲም ምንዛሪው ስንት እንደሚሆን ግለጽ | በባለ 5 ሣንቲም ምንዛሪው ስንት እንደሚሆን ግለጽ | በባለ 10 ሣንቲም ምንዛሪው ስንት እንደሚሆን ግለጽ | በባለ 25 ሣንቲም ምንዛሪው ስንት እንደሚሆን ግለጽ |
|---|---|---|---|---|
| **50 ሣንቲም** | **50** | **10** | **5** | **2** |
| **25 ሣንቲም** | | | | |
| **10 ሣንቲም** | | | | |
| **5 ሣንቲም** | | | | |

## የብር ኖቶች

**የሚከተሉት የኢትዮጵያ የብር ኖቶች ምሥሎች ናቸው።**

| | | |
|---|---|---|
|  |  |  |
| የአንድ ብር ኖት | የአምስት ብር ኖት | የአሥር ብር ኖት |
|  |  | |
| የ50 ብር ኖት | የ100 ብር ኖት | |

## የክፍል ሥራ

የሚከተሉትን የኢትዮጵያ የብር ኖቶች ሥም ፃፉ።

| | | |
|---|---|---|
|  |  |  |
| | | |

| | | |
|---|---|---|
|  |  |  |
| | | |

**መልመጃ**

ሠንጠረዡን በምሳሌው መሠረት ሙሉ።

| የተሰጠው የብር ኖት | ምንዛሪ | | | |
|---|---|---|---|---|
| | በባለ 1 ብር ኖት | በባለ 5 ብር ኖት | በባለ 10 ብር ኖት | በባለ 50 ብር ኖት |
| ባለ 100 ብር | 100 | 20 | 10 | 2 |
| ባለ 50 ብር | | | | |
| ባለ 10 ብር | | | | |
| ባለ 5 ብር | | | | |

# 10.2 የሣንቲሞችና የብር ኖቶች ዝምድና

የብር ኖቶች በሣንቲሞች ሊመነዘሩ ይችላሉ።

**ምሳሌ**

1. አንድ የ1 ብር ኖት በ4 የ25 ሣንቲም ዲናሮች ይመነዘራል። እንዲሁም ይኸው የ1 ብር ኖት በ10 የአሥር ሣንቲም ዲናሮች ሊመነዘር ይችላል።
2. በተመሳሳይ መልክም አንድ የ5 ብር ኖት በ10 የ50 ሣንቲም ዲናሮች ሊመነዘር ይችላል።

## የቡድን ሥራ ❶

1. የሚከተለውን ሠንጠረዥ አጥኑ

| የብር ኖት | ባለ 1 ሣንቲም ዲናሮች | ባለ 5 ሣንቲም ዲናሮች | ባለ አሥር ሣንቲም ዲናሮች | ባለ 25 ሣንቲም ዲናሮች | ባለሃምሣ ሣንቲም ዲናሮች | ባለ 1 ብር ሣንቲም ዲናሮች |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 100 | 20 | 10 | 4 | 2 | 1 |
| 5 | | 100 | 50 | 20 | 10 | 5 |
| 10 | | | 100 | 40 | 20 | 10 |

2. የሣንቲምና የብር ኖት ሞዴሎችን ከወረቀት ወይም ከሌላ በአካባቢው ከሚገኝ ምቹ ነገሮች ሥሩ፡፡

3. በነዚህ ሞዴሎች በመጠቀም በምንዛሪዎች ላይ ከላይ ከተሰጠው ሠንጠረዥ ጋር በማዛመድ ተወያዩ፡፡

4. ከላይ በቁጥር 2 ላይ በሠራችኋቸው ሞዴሎች በመጠቀም ከቡድናችሁ አባላት አንዳችሁ ሻጭ በመሆንና ሌሎቻችሁ ገዥ በመሆን የመማሪያ ቁሳቁሶቻችሁን በሻጭና በገዥ መልክ ተለዋወጡ፡፡ የሚከተለውን የዋጋ ተመንም ተጠቀሙ፡፡

   1 ደብተር --------------------- 3 ብር

   1 የሒሳብ መጽሐፍ ------ 18 ብር

   1 እርሳስ -------------------- 50 ሣንቲም

   1 እስክርቢቶ ---------------- 1 ብር ከ50 ሣንቲም

## የማጠቃለያ መልመጃ

### ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጡ፡፡

1. አንድ የመቶ ብር ኖት
   ሀ. በስንት የ5 ብር ኖቶች ይመነዘራል?
   ለ. በስንት የ50 ብር ኖቶች ይመነዘራል?
2. አንድ የ10 ብር ኖት
   ሀ. በስንት የባለ 50 ሣንቲም ዲናሮች ይመነዘራል?
   ለ. በስንት የባለ 25 ሣንቲም ዲናሮች ይመነዘራል?
   ሐ. በስንት የባለ 10 ሣንቲም ዲናሮች ይመነዘራል?
3. አንድ ባለ 5 ብር ኖት
   ሀ. በስንት የባለ 10 ሣንቲም ዲናሮች ይመነዘራል?
   ለ. በስንት የባለ 25 ሣንቲም ዲናሮች ይመነዘራል?
   ሐ. በስንት የባለ 50 ሣንቲም ዲናሮች ይመነዘራል?

© MoE Ethiopia Not to be Published